የሰ/መ/ቁ. 66856

የመጋቢት 26 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሤ

**አመልካች፡-** ውድማ አበጆ - አልቀረበም፡፡

**ተጠሪ፡-** የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ዐ/ሕግ አልቀረበም፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን፣ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር ጉዳይ የቀረበው የአንድ የወንጀል አፈፃፀም ተግባር በሙከራ ደረጃ ላይ ደርሷል የሚባለው መቼ፤ እንዴት ነው? የሚለውን ነጥብ በዚህ የወንጀል ጉዳይ በማስረጃ ከተረጋገጡት የፍሬ ነገር ጉዳዮች ጋር በማናገዘብ ተገቢውን ዳኝነት ለመስጠት በሚል ነው፡፡

የጉዳዩ መነሻ በክልሉ የጉራጌ ዞን ዐ/ሕግ በአሁኑ አመልካችና በግብረ-አበሮቹ ላይ ሦስቱም ተከሳሾች በወ/ህ/ቁ 32/1/ /ሀ/፣ 27/1/ እና 671/1/ለ ሥር የተመለከተውን ድንጋጌ በመተላለፍ በጅማ ወለኔ ቀበሌ የሚመላለሱትን ተሽከርካሪዎች ለመዝረፍ የጦር መሣሪያ፣ ጭንብል፣ የእጅ ባትሪ፣ ጩቤ በመያዝ ከመጋቢት 07 ቀን እስከ መጋቢት 08 ቀን 2001 ዓ.ም ድረስ ተንቀሳቅሰው ጠብቀው ተሽከርካሪ በማጣታቸው ሲመለሱ በተደረገው ጥቆማ መነሻ በፀጥታ ኃይሎች ስለተያዙ በፈፀሙት ከባድ የውንብድና ሙከራ ወንጀል ተከሰዋል በማለት ያቀረበው ክስ ሲሆን፤ የአሁን አመልካች በተከሳሽነቱ ድርጊቱን አልፈፀምኩም፤ ጥፋተኛም አይደለሁም በማለት ክዶ ተከራክሯል፡፡

በማስረጃነትም የሰው ማስረጃና ተከሳሾች በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 27 እና 35 መሠረት በምርመራ ጊዜ ለመርማሪ ፖሊስ እና በፍ/ቤት የሰጡት ቃል ቀርቧል፡፡ በሰው ማስረጃው የተረጋገጠው መጋቢት 07 ቀን 2001 ዓ.ም ከአንድ የመኪና አሽከርካሪ ሽፍቶች ለመዝረፍ ተሰማርተዋል የሚል ጥቆማ አግኝቼ ወዲያውኑ ስከታተል ማግኘት አልቻልኩም፡፡ ተሽከርካሪ በማስቀም በተደረገው ጥብቅ ክትትል እነዚህ ሦስት ሰዎች መታወቂያ ሲጠየቁ የላቸውም፡፡ በግንባታ ሥራ ተሰማርተን የግንባታ ቁሳቁስ እጥረት ስለአጋጠመ ወደ መኖሪያችን እየሄድን ነው አሉ፡፡ ዕቃቸው ሲፈተሽ ግን አንድ የጦር መሣሪያ፣ ጩቤ፣ ጭንብል ተገኝቶባቸዋል የሚል ነው፡፡ እንዲሁም በምርመራ ጊዜ በሰጡት የእምነት ቃልም ለዘረፋ ተስማምተው አስፈላጊውን ቅድመ-ዝግጅት አድርገው ያመቺናል ብለው ወደ አሰቡበት ቦታ በመሄድ ጫካ ውስጥ ከአደሩ በኂላ ባገኙት

መኪና ተሳፍረው ሲመለሱ ከያዙት የዘረፋ ቁሳቁስ ጋር በፖሊስ ቁጥጥር ሥር መዋላቸውን የሚገልፅ ነው፡፡

ፍ/ቤቱም ይህንኑ የዐ/ሕግ ማስረጃ እና ተከሳሾች እንከላከላለን ሲሉ ያቀረቡትን ማስረጃ በማገናዘብ ከመረመረ በኋላ እንደ ክሱ አቀራረብ ጥፋተኛ ናቸው ካለ በኋላ ከሦስተኛው ተከሳሽ በስተቀር በአሁን አመልካችና ሁለተኛ ተከሳሽ በነበረው ሌላ ግብረአበር ላይ የቀረበውን የወንጀል ጥፋተኝነት እና ቅጣት ሪከርድ መነሻ በማድረግ በአሁን አመልካች ላይ የ22 ዓመት ፅኑ እስራት ቅጣት ጥሏል፡፡

ከዚህም ቀደም ብለው መግደል ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከተባለበት ፅኑ እስራት የ10 ዓመቱን በእስር ሊጨርስ በሚል በአመክሮ መለቀቁን መነሻ በማድረግ የተጣለ ቅጣት እንደሆነ የውሳኔው ግልባጭ ያስረዳል፡፡

በዚህ ውሳኔ ላይ በደረጃው ላሉ የበላይ ፍ/ቤቶች እንዲታረም ቅሬታ ቢያቀርብም ቅሬታው ውድቅ በመደረጉ ለመጨረሻ ጊዜ ጉዳዩን በዚህ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡

በዚህ ችሎት ግራ ቀኙ ክርክር ያደረጉበት ነጥብ ይህ አመልካች እና ሌሎች ግብረ-አበሮች የፈፀሙት ተግባር በሙከራ ወንጀል ሥር ሊወድቅ የሚችል ነው ወይስ አይደለም? በሚለው ላይ ነው፡፡ እኛም በዚሁ ጭብጥ ላይ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ቅሬታ ከሥር ፍ/ቤቶች የውሳኔ ግልባጭ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነውም በ1997 ዓ.ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 27 እንደተደነገገው ማንም ሰው አስቦ ወንጀሉን ማድረግ ጀምሮ የወንጀሉን ድርጊት እስከመጨረሻው ባይከታተልም ወይም ለመከታተል ባይቻልም የወንጀል ድርጊቱ እንዲፈፀም እስከመጨረሻው ተከታትሎ አስፈላጊ የሆነውን ውጤት ያላስገኘ ቢሆንም የሙከራ ወንጀሉን እንደፈፀመ እንደሚያስቆጥረው ተመልክቷል፡፡

በዚህም ጉዳይ በፍሬ ነገር ረገድ እንደተረጋገጠው ከድርጊቱ በፊት ተከሳሾች ሁልጊዜ የዘረፋ ወንጀል በሚፈፀምበት ጫካ መግባታቸው፤ ይህን በተመለከተ በሰው ጥቆማ አማካኝነት በፀጥታ ኃይሎች በተደረገው ክትትል ተሳፍረውበት ከነበረው መኪና ከጦር መሣሪያ፣ ጩቤና ጭንብል ጋር መያዛቸው፤ እንዲሁም በእራሳቸው የእምነት ቃል እንደተረጋገጠው ለዘረፋ ወንጀል አስፈላጊውን ቅድመ-ዝግጅት አጠናቀው ከዚሁ ጫካ ውስጥ ሲጠባበቁ አድረው በማግስቱ በመኪና ተሳፍረው ሲሄዱ ለዘረፋ ተግባር ሲሉ ከያዙት ቁሳቁስ ጋር መያዛቸው ሁሉ ሲታይ አመልካችና ግብረ-አበሮቹ የዘረፋ ወንጀል ለመፈፀም እስከመጨረሻው ተከታትለው ነገር ግን የሚዘረፍ ነገር ባለማግኘታቸው ውጤቱን ያላገኙ መሆኑን አስረጂ ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ በአመልካችና በግብረ-አበሮቹ በኩል የተፈፀመው ተግባር በእራሱ የዘረፋ ወንጀሉን ለመፈፀም ወደ ኋላ ከማይመለሱበት ደረጃ ደርሰው የነበረ መሆኑን አመላካች ነው፡፡ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቱ ይህንን ሁሉ በማገናዘብ የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ አመልካች ተላልፎታል ተብሎ በተጠቀሰው ሕግ አነጋገር መሠረት ሆኖ የተገኘ እንጂ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ባለመሆኑ የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁ 33619 በቀን 12/06/2002 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/2/ /ለ/ /2/ መሠረት ፀንቷል፡፡ አመልካች ይህንኑ እንዲያውቀዉ ውጤቱ ባለበት ማ/ቤት ይገለፅለት፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/መ